# እሪ በይ አገሬ

እሪ በይ ኢትዮጵያ ፤ ቅል ድንጋይ ሰበረ
ውሃ ሽቅብ ወጣ ፤ ዘመን ተቀየረ
ሌባ እየከበረ ፤ ነጋዴው ከሰረ
አገር ፈራረሰች ፤ ድንበር ተደፈረ
እንደ ቅርጫ ሥጋ ፤ እየተመተረ
ላረብ ለድርቡሹ ፤ ይታደል ጀመረ
ጀግና አንገቱን ደፋ ፤ ባንዳ ተወጠረ
ትንሹም ትልቁም ፤ አይኖቹ ታወረ
በደሃው ትከሻ ፤ ከሃዲው ከበረ
ዘርፎ መብላት እንጂ ፤ ሰርቶ ማደር ቀረ
ከድጡ ወደ ማጡ ፤ እየተነከረ
ከሳት ወደረመጥ ፤ እየተጨመረ
በጎጥና በዘር ፤ አምልኮ ሰከረ
ከናት ካባቶቹ ፤ መቼም አልተማረ
ህያው መስሎ ይታያል ፤ እየተቀበረ
የሀገር ምሰሶው ፤ ዋልታው ተሰበረ ።

እሪ በይ ኢትዮጵያ ፤ ጩኸትሽን አሰሚ
እንዴት በወያኔ ፤ በባንዳ ትደሚ
ያውም በአልበሽር ፤ አሽርጋጅ ከዳሚ
በሹምባሽ አጎንባሽ ፤ ክብርሽን ትቀሚ
የንግዴን ልጅማ ፤ ይብቃሽ አታስታሚ
ሰቆቃው በዛብኝ ፤ ብለሽ ተቃወሚ
ወንበዴም ይሽበር ፤ አንቺም አግኝ ሰሚ ።

እሪ በይ አገሬ ፤ እሪታ ነው ደጉ
በዐረብ ምጽዋት ፤ ዳረጎት ያደጉ
ደደቢት ዋሻቸው ፤ ገብተው ይሽሹጉ
እንዳበደ ውሻ ፤ ይቅበዝበዙ አይርጉ
ይሽበር ወያኔ ፤ ይውጡ ይጠረጉ
አመጽ በሽታው ነው ፤ ይታይለት ሰርጉ
ተረግጦማ አይቀርም ፤ ክብርሽ ማዕረጉ ።

እሪ በል ያገር ልጅ ፤ ተነስ ዳር እስከ ዳር
ይንደድ ይቀጣጠል ፤ ያመጽ ክብሪት ይጫር
ትግልህን አጠንክር ፤  አምባገነን ይሻር
ጠላት ካልረገጡት ፤ ምንግዜም አይማር ።

ታዛቢው